የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ

ህዳር 2011 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ

ህዳር 2011 ዓ.ም

# ማውጫ


**1. መግቢያ ........ 1**

**2. የፖሊሲው አስፈላጊነት........ 4**

**3. ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ ግብና ዓላማዎች ........ 6**

3.1 ተልዕኮ ........ 6

3.2 ራዕይ ........ 6

3.3 ግብ........ 6

3.4 ዓላማዎች........ 6

**4. የፖሊሲው ወሰን........ 8**

**5. የፖሊሲው ማዕቀፍ........ 9**

**6. የፖሊሲው እሴቶችና መርሆዎች........ 10**

6.1. እሴቶች ........ 10

6.2. መርሆዎች ........ 11

**7. የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ አቅጣጫዎች........ 12**

7.1 የተመጣጠነ፣ በንጥረ-ምግብ ይዘታው የበለፀገና ደህንነቱ የተረጋገጠ ምግብ አቅርቦት፤ ተደራሽነትና አጠቃቀምን በዘላቂነት ማረጋገጥ........ 12

7.2. ከእርሻ እስከ ጉርሻ የምግብ ደህንነትና ጥራት........ 13

7.3 የድህረ-ምርት አያያዝ ........ 15

7.4 በሁሉም የእድሜ ክልል ለሚገኙ ሰዎች ተገቢ ሥርዓተ-ምግብን ማረጋገጥ ........ 16

7.5 ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ምላሽ ........ 18

7.6 የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተግባቦት ማጠናከር ........ 19

7.7 የምግብና ሥርዓተ-ምግብ አስተዳደር........ 20

**8. የፖሊሲው ትግበራ ........ 22**

8.1 አካሄዶች ........ 22

8.1.1 የሕይወት ኡደት አካሄድ ........ 22

8.1.2. ምግብ እንደ ሰብአዊ መብት ........ 23

8.1.3. ምግብን መሰረት ያደረገ አካሄድ ........ 23
8.1.4. የተለያዩ-ሴክተሮች ትብብር፣ ቅንጅትና ትስስር ........ 23
8.1.5. ቀጥተኛና የሥርዓተ-ምግብ ተኮር ተግባራት ........ 24
8.1.6. ከእርሻ እስከ ጉርሻ ........ 24
8.2. የህግ ማዕቀፍ ........ 25
8.3. ተቋማዊ አደረጃጀት ........ 25
8.4. የአቅም ግንባታ ........ 26
8.4.1 የሰው ኃይል ........ 26
8.4.2. የስልጠናና ምርምር ተቋማት ........ 28
8.4.3. ቁጥጥር አካላት ........ 28
8.5. የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተግባቦት ........ 29
8.6. ዘላቂ የገንዘብ ምንጭ ........ 30
**9. ለሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ምላሽ ሰጭነት ........ 31**
**10. የባለ ድርሻ አካላት ........ 33**
10.1 የመንግስት ........ 33
10.2 መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ........ 33
10.3 የግል ባለሃብቱ ሚና ........ 33
10.4. የህብረተሰቡ ሚና ........ 34
**11.ክትትልና ግምገማ ........ 35**
**12.የቃላት ፍቺዎች ........ 37**

# 1 መግቢያ

በአንድ ሀገር ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ለማምጣትና ዘላቂ የልማት አቅም ለመገንባት ለዜጎች በማንኛውም ጊዜ የምግብ አቅርቦትና ተደራሽነትን ማረጋገጥና ጥራቱ፣ ደህንነቱና የንጥረ - ምግብ ይዘቱ የተሟላ ምግብ የሚመገብ ጤናማ፤ አምራች፤ ረዥም ዕድሜና አስተማማኝ የፈጠራ ብቃት ያለው ዜጋ መገንባት ወሳኝ ነው። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በሁሉም ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ዜጎች ጤናማ ህይወት እንዲኖራቸው የማህበረሰቡን የተመጣጠነ ምግብ ዕውቀትና የምግብ አጠቃቀምን ማሳደግ፤ የምግብ ስርጭት ሰንሰለት ውስጥ የምግብ ጥራትና ደህንነትን ማረጋገጥ፤ የምግብና የንጥረ-ምግብ ብክነትን መቀነስና የምግብና ሥርዓተ-ምግብ አደጋን የመከላከል ዝግጁነትንና የመቋቋም አቅምን ማሳደግ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም የምግብና ሥርአተ-ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችል አግባብነት ያለው ፖሊሲ መኖር እንደ ዋነኛ መሰረታዊ ግብዓት ይወሰዳል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ላለፉት አስርት ዓመታት የተቀናጁና ሥር-ነቀል ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በመተግበር አዎንታዊ የማህበራዊና የምጣኔ ሀብት ዕድገት አስመዝግቧል። ይህንን ለማስቀጠልና ፅኑ የሆነ የኢኮኖሚ መሰረት ለመጣል የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። በመሆኑም የሀገሪቱን ሁሉን አቀፍ ዕድገት የበለጠ ለማፋጠን አዋጭና ዘለቄታ ያላቸው የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አማራጮችን ተግባራዊ ማድረግ ትኩረት የሚሹ መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው።

በዚሁ መሰረት የሀገሪቱን የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በርካታ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። ለአብነትም ያህል አርሶና አርብቶ አደሮችን በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት፣ በእንስሳትና ዓሣ ሀብት መስክ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር የተደረጉ ጥረቶች የሚጠቀሱ ናቸው። በሀገሪቱም በተለያዩ ጊዜያት ያጋጠሙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አደጋዎችን በራስ አቅም መከላከል መቻሉ አደጋዎችን የመቋቋም አቅም ማደጉን የሚያመላክት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዙሪያ በተሰሩ ስራዎች የህፃናትን መቀንጨር ከ58 በመቶ ወደ 38.4 በመቶ መቀነስ የተቻለ ሲሆን የመክሳት ችግርን ደግሞ ከ41 በመቶ ወደ 23.6 በመቶ እንዲቀንስ ለማድረግ ተችሏል። እንዲሁም የመቀጨጭ ችግር ከ12 በመቶ ወደ 9.9 በመቶ ሊቀንስ ችሏል። ከዚህም ባሻገር በህይወት ከሚወለዱ 1000 ህፃናት መካከል አምስት አመት ሳይሞላቸው ይሞቱ ከነበሩት ህፃናት ከ166 ወደ 67 በመቀነስ ለምዕተ ዓመቱ ግቦች መሳካት የሥርዓተ-ምግብ በጎ ለውጦች አስተዋፅኦ አድርገዋል። በተጨማሪም የዜጎች የዕድሜ ጣሪያ ከ45 ዓመት ወደ 64 ዓመት ከፍ ለማድረግ ተችሏል::

ይሁን እንጂ የሀገሪቱ የምግብ ምርት ዕድገት ከሀገሪቱ የህዝብ ዕድገት ጋር ሲነፃፀር ያነሰ በመሆኑ የህብረተሰቡን የምግብ ፍላጎት ለማሟላት ባለመቻሉ በሁሉም የዕድሜ ክልልና የአኗኗር ሁኔታዎች የሚገኙ ዜጎች ለምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትና ችግርና ለጊዜያዊ ተረጂነት እየተጋለጡ ይገኛሉ። በዚህም መሰረት በሀገር አቀፍ ደረጃ አርባ በመቶ የሚሆኑ ቤተሰቦች ከምግብ መገኘት ላለበት የሀይል እጥረት የተጋለጡ ሲሆን ይህም ሀምሳ በመቶ የሚሆኑ ቤተሰቦች የሀይል ምንጫቸው ከእህል ከሚዘጋጁ ምግቦች ብቻ በመሆኑ ነው። በተጨማሪም ዝቅተኛ ምርትና ምርታማነት፣ ደህንነቱንና ጥራቱን ያልጠበቀ የምርት ሂደት፣ ደካማ የቅድመና የድህረ-ምርት አያያዝ፣ ዝቅተኛ የእናቶችና የህፃናት እንክብካቤ፣ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትና ተጠቃሚነት እንዲሁም ከፍተኛ የግልና የአካባቢ ንፅህና ጉድለት ሀገሪቱን በዋናነት ለከፍተኛ የምግብና

ሥርዓተ-ምግብ ዋስትና ችግሮች እየዳረጓት ይገኛሉ። በመሆኑም ይህ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ ሀገሪቱ እያጋጠሟት ያሉትን የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትና ተግዳሮቶችን ለመፍታት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ በሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ቅንጅትና ትብብር እንዲተገበር በተለያዩ ደረጃ ያሉ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ተዘጋጅቷል።

# 2 የፖሊሲው አስፈላጊነት

የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሰው ልጅ ሰብዓዊና ህገ-መንግስታዊ መብት ሲሆን መንግስትም ይህንን የዜጎች መብት የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል። በሃገራችን የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተቀረፁት ስልቶችና ፕሮግራሞች ማለትም የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ፤ ብሔራዊ የሥርዓተ-ምግብ ስትራቴጂ፤ ብሔራዊ የሥርዓተ-ምግብ ፕሮግራምና የሰቆጣ ቃልኪዳን የብዙ ሴክተሮችን ባለቤትነት፣ ቅንጅትና ትስስር የሚጠይቁ ሆነው እንዲተገበሩ የተደረገ ቢሆንም የህግ ማዕቀፍና የተግባሪ ሴክተሮችን ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ ሥርዓት ባለመዘርጋቱ በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት ውጤት ለማምጣት አልተቻለም።

የምግብ እጥረትና ሥርዓተ-ምግብ አለመመጣጠን ችግሮችን መከላከል ካልቻልን ህብረተሰቡ ለተደጋጋሚ በሽታና ሞት ይጋለጣል። በተለይም በዚህ ችግር የተጎዱ እናቶች የቀጨጩ እንዲሁም ክብደታቸው የቀነሰ ከመሆኑም ባሻገር ለደም ማነስና በወሊድ ጊዜ ለሚከሰቱ ችግሮች የድህረ ወሊድ የደም መፍሰስና ሌሎች ችግሮች ተጋላጭ ይሆናሉ። ከነዚህም እናቶች የሚወለዱ ህፃናት ክብደታቸው ያነሰና የቀነጨሩ በመሆናቸው በቀላሉ በተደጋጋሚ በበሽታ የሚጠቁና ያለዕድሜያቸው ህይወታቸው የሚቀጠፍ ከመሆኑም በላይ ችግሩ በአዕምሮአዊና አካላዊ ዕድገታቸው ላይ ተጽዕኖ በማሳደር ዝቅተኛ የትምህርት አቀባበል፣ አዳዲስ ነገሮችን የማፍለቅ ችሎታ ውስንነትና በሚሰማሩበት ዘርፍ ሁሉ ብቁ፣ ውጤታማና አምራች ዜጋ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ የመቀንጨር አለመቀነስና ሥር-ሰደድ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ስርጭት መጠን እየጨመረ መምጣቱ ሀገሪቱ ላይ መንታ ገፅታ ያለው የሥርዓተ-ምግብ መዓደል ችግሮች ጫናን በማሳደር አጠቃላይ ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነስ የሰው ሃይል ልማትንና የሀገሪቷን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳል።

የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሀገሪቱ ተቀዳሚ የልማት አጀንዳ ሲሆን፤ የዘርፈ-ብዙ ምላሽ ቅንጅትና ትስስር፣ የተጠያቂነትና የህግ ማዕቀፍ ሲዘጋጅ፣ በቂና ዘላቂ መዋዕለ ንዋይ መመደብ ሲቻል፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ሲቻል፣ አመጋገብን ማዕከል ያደረገ የሰው ሃብት ልማት ሲኖር ለምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትና መረጋገጥና ዘላቂነት መሰረት ይጥላል። ስለዚህ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲው መዘጋጀት የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ የዜጎችን የመልካም ህይወትን፣ ምርታማነትንና ረዥም ዕድሜ መኖርን በማረጋገጥ ለሀገር ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልጽግና አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ያስችላል። በተጨማሪም ተለይተው የተቀመጡ ወሳኝ ተግባሮችን ፖለቲካዊ አንድምታ በመስጠት የተግባሪ ሴክተር መስሪያ ቤቶችንና ባለድርሻ አካላትን በኃላፊነትና በተጠያቂነት ለመምራትና ለማስተባበር እንዲያስችል ይህ ብሔራዊ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ ማውጣት አስፈልጓል።

# 3 ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ግብና ዓላማዎች

## 3.1 ራዕይ

የሥርዓተ-ምግብ ዋስትናቸው የተረጋገጠ፣ ጤናማ ህይወት ያላቸው፣ አምራችና እድሜ ጠገብ ኢትዮጵያውያንን ማየት ነው።

## 3.2 ተልዕኮ

ቀጥተኛና ሥርዓተ-ምግብ ተኮር ሴክተሮች ቅንጅታዊ አሰራርን በማረጋገጥ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትናን ማስፈን ነው።

## 3.3 ግብ

በሁሉም ዕድሜ ክልልና ሁኔታ ለሚገኙ ዜጎች ጤናማ ህይወት፣ አምራችነትና ረዥም እድሜ እንዲኖራቸው የሚያስችል የሥርዓተ-ምግብ ደረጃ ላይ ማድረስ ነው።

## 3.4 ዓላማዎች

የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ ዓላማዎች ምቹ የፖሊሲ ሁኔታን በመፍጠር፡-

1. ለሁሉም ዜጎች በማንኛውም ጊዜ በቂ የምግብ አቅርቦትና ተደራሽነትን ማረጋገጥ።

2. በማንኛውም የህይወት ኡደት ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች ጥራቱ የተረጋገጠ የሥርዓተ-ምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተኮር የጤና አገልግሎቶችን ተደራሽነትና ፍትሃዊነት ማሻሻል።

3. በሁሉም እድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች ጤናማ ህይወት እንዲኖራቸው የሚያስችል የተመጣጠነ አመጋገብና የሰውነት ንጥረ - ምግብ አጠቃቀምን ማሻሻል።

4. በሁሉም የምግብ ስርጭት ሰንሰለት ውስጥ የምግብን ጥራትና ደህንነትን ማረጋገጥ።

5. በሁሉም የምግብ ስርጭት ሰንሰለት ውስጥ የምግብና የንጥረ-ምግብ ብክነትን መቀነስ።

6. የምግብና ሥርዓተ-ምግብ አደጋ የመከላከል፣ ዝግጁነትና የመቋቋም ሥርዓትን ማሻሻል።

7. በምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዙሪያ የዜጎችን ዕውቀት ማሻሻል።

# 4 የፖሊሲው ወሰን

ፖሊሲው "የኢትዮጵያ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ" ተብሎ ይጠራል። መነሻ ያደረገውም የህግና የሥነ-ምግባር መሰረት በሆነው በሀገሪቱ ህገ-መንግሥት የሰፈረውን የዜጎችን ደህንነትና መብት ማስጠበቅ ሲሆን አዘገጃጀቱም ከሴክተሮች ፖሊሲዎችና ስልቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ ነው። የፖሊሲው ወሰን ሰፋ ያለ ሲሆን ለሴክተሮች ቅንጅት፤ ሕብረተሰብ ተኮር የሥርዓተ-ምግብ ትግበራ፤ ውጤታማ የሥርዓተ-ምግብ ተኮር ዘርፎች ተግባራትን ለማበረታታትና ተያያዥነት ያላቸውን የትግበራና አስተዳደራዊ ስልቶችን ለመዘርጋት የፖሊሲ መሰረት ይሰጣል።

ፖሊሲው ሁሉንም ቁልፍ የሆኑ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ክፍሎች ማለትም ዘላቂ የምግብ አቅርቦት፣ ተደራሽነትና አጠቃቀም፤ የምግብ ጥራትና ደህንነት፤ ድህረ-ምርት አያያዝ፤ ተገቢ የምግብና የሥርዓተ-ምግብ ዋስትና በሁሉም ማህበረሰብ ደረጃ፣ መልክዓ-ምድር፤ አካባቢና የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም በአደጋ ጊዜ እንዲረጋገጥ ማዕቀፍ ይሰጣል። በተጨማሪም ፖሊሲው ለመሬት መሸርሸር፣ ሉዓላዊነት፣ የአህጉራዊ የገበያ ጥምረት፣ የሥነ-ህዝብ ለውጥ፣ የገቢ አለመመጣጠን፣ የህዝብ ብዛት ጫና፣ የከተሞች መስፋፋትና ለተፈጥሮ ሀብት ያለው ፍላጎት መጨመርን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን ለሀገራዊ፣ ክልላዊና ተቋማዊ አቅም ግንባታም ትኩረት ይሰጣል። እንዲሁም ህብረተሰቡን በማበረታታት የግለሰቦችና የቤተሰብ መልካም የአመጋገብ ተግባራት እንዲዳብሩና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮችን በሀገር አቀፍ፣ በክልልና በህብረተሰቡ ደረጃ ከእርሻ እስከ ጉርሻና በህይወት ዑደት መርሆ መሰረት መፍትሄ ለመስጠት ለሚደረጉት ጥረቶች አጠቃላይ ማዕቀፍ ይሰጣል።

# 5 የፖሊሲው ማዕቀፍ

ይህ ፖሊሲ በተለያዩ ደረጃዎች የሚስተዋለውን የሥርዓተ-ምግብ አለመረጋገጥ መንስዔዎችን ለመፍታት ዓለም አቀፋዊ የንድፈ ሃሳብ ማዕቀፍን መሰረት ያደርጋል። የፖሊሲው ማዕቀፍ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ስልቶችን አቀናጅቶ በመጠቀም በተለያዩ ደረጃዎች የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታት ላይ ያተኩራል። ለሥርዓተ-ምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ እንደ ቀዳሚ መንስኤዔ የሚወሰዱት የንጥረ-ምግብ አወሳሰድ አለመመጣጠንና የጤና መጓደል ናቸው።

በተመሳሳይ ሁኔታ የመካከለኛ ደረጃ የሥርዓተ-ምግብ አለመረጋገጥ መንስኤዔዎች የግብርና ልማዳዊ አሰራሮች እንዲሁም የንጹህ የመጠጥ ውሃና የአካባቢ ንጽህና አቅርቦትና ተደራሽነት ዝቅተኛ መሆን፤ የጤና አገልግሎቶች፣ የሴቶች ትምህርትና ሥርዓተ-ጾታ ተኮር የድጋፍ ተግባራት፣ ማህበራዊ እንክብካቤና ማህበራዊ ሴፍቲኔት አቅርቦትና ተደራሽነት ዝቅተኛ መሆን ይገኙበታል። እንደ መሰረታዊ የሥርዓተ-ምግብ መረጋገጥ መንስኤ ተደርገው ከሚወሰዱት ውስጥ ደግሞ ከተቋማዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ያላቸው እንደ ድህነት ቅነሳ፣ ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት፣ መልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ብቃቶች፣ መሰረታዊ ትምህርት፣ የግብርና፣ የመስኖና ሌሎች መሰረተ ልማቶች አለመሟላት ይገኙበታል።

# 6 የፖሊሲው እሴቶችና መርህዎች

## 6.1 የፖሊሲው እሴቶች

ፖሊሲው የሚከተሉትን እሴቶች ከግምት ውስጥ ያስገባል።

1. **ሕብረተሰቡን ማዕከል ማድረግ** – የህብረተሰቡን እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ቅድሚያ መስጠት።

2. **ቅንጅታዊነት** – ሁሉም ባለድርሻ አካላት በፖሊሲው ትግበራ ላይ በተቀናጀ መልኩ እንዲሳተፉ ማድረግ።

3. **ተጠያቂነት** – ለስራዎች ቁርጠኛ መሆንና ኃላፊነት በመውሰድ ግልፀኝነት በተሞላበት አግባብ ውጤቶችንም ማሳወቅ።

4. **ፍትሃዊነት** – በሴክተር፣ በፆታ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በዕድሜ፣ በመልክዓ-ምድር፣ በማህበራዊ ቀውስ፣ በአኗኗር ዘይቤና በመሳሰሉት ሁኔታዎች የሚፈጠሩ ተጋላጭነቶችንና ልዩነቶችን ማጥበብ።

5. **ምላሽ ሰጪነት** - የማህበረሰቡን የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፍላጎት ለሟሟላት ፈጣንና አዎንታዊ ምላሽ መስጠትና ለማንኛውም የምግብ እጥረት ተጋላጭነትን የመቋቋም አቅምን ማረጋገጥ።

## 6.2 መርሆዎች

የምግብና የሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲው በሚከተሉት መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ነው።

1. የሕይወት ዑደትን መከተልና በተለይም የመጀመሪያዎቹ 1000 ቀናት ወሳኝ መሆናቸውን የሚቀበል መሆኑ፤

2. በቂ፣ ደህንነቱና ጥራቱ የጠበቀ ምግብ ተደራሽነት ሰብአዊ መብት መሆኑንና ህብረተሰቡ ተአማኒነት ያለው መረጃ ላይ በመመስረት ትክክለኛ የምግብ ምርጫ እንዲኖረው የማድረግ መብት የሚያረጋግጥና ውሳኔ የሚሰጥ ማዕቀፍ የሚያስቀምጥ መሆኑ፤

3. የምግብና የሥርዓተ-ምግብ ጉዳዮች ሴክተር ተሻጋሪ መሆናቸውን የሚገነዘብና በሴክተሮች መካከልው ጤታማ ቅንጅታዊ አሰራርን የማዳበር አስፈላጊነትን የሚደግፍ መሆኑ፤

4. በምግብና በአመጋገብ ሥርዓቶች ላይ በሕብረተሰቡ ውስጥ ለሚገኙ ሀገር በቀል ዕውቀቶችና ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮዎችን በመቀመርና የህብረተሰቡን አመጋገብ ስርዓት ታሳቢ በማድረግ ዘላቂ የምግብ ሰንሰለት የሚያበረታታ መሆኑ፤

5. በሀገሪቱ የምግብ ሉዓላዊነትን በማረጋገጥ በምግብ እሴት ሰንሰለት ውስጥ የመንግሥትና የግል ባለሀብቱን የጋራ ኃላፊነት የሚያበረታታ መሆኑ፤

6. ምግብን እንደ ስትራቴጂያዊ ሀብት በመገንዘብ አዳዲስ ምግቦችን ለማዘጋጀት፣ ለማቀነባበርና ለማላመድ የሚረዱ አዳዲስ፣ አዋጭና ለአካባቢ ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን መፍጠርና ስራ ላይ ማዋልን የሚደግፍ መሆኑ።

# 7 የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ አቅጣጫዎች

## 7.1. የተመጣጠነ፣ በንጥረ-ምግብ ይዞታው የበለፀገና ደህንነቱ የተረጋገጠ ምግብ አቅርቦት፤ ተደራሽነትና አጠቃቀምን በዘላቂነት ማረጋገጥ

የምግብ ዋስትናን በዘላቂነት ማረጋገጥ የሚቻለው ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፤ የምግብ አቅርቦትን በመጨመር፤ የምግብ ተደራሽነትን በማረጋገጥ፤ የምግብ ብክነትን በመቀነስና ንጥረ ምግቦች በሰውነት ውስጥ ጥቅም ላይ ውለው የተሟላ ጤናና ደስታን እንዲያጎናፅፉ በማድረግ ነው። የኢትዮጵያ መንግስት የምግብ ዋስትና መሰረታዊ የሰብአዊ መብት መሆኑን ስለሚገነዘብ የምግብ ዋስትና አንዱ የፖሊሲ አቅጣጫ እንዲሆን ተደርጓል።

### ዓላማ

ፖሊሲው የሚከተለው ዓላማ ይኖረዋል።

1. በቂ፤ የተመጣጠነ፣ በንጥረ-ምግብ ይዘቱ የተሟላና ደህንነቱ የተረጋገጠ ምግብ አቅርቦትንና ተደራሽነትን ለዜጎች በዘላቂነት ማሻሻል።

### ስልቶች

ከላይ የተጠቀሰውን ዓላማ ለማሳካት መንግሥት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገብራል።

1. የእርሻ፣ እንስሳትና ዓሳ ሀብት ምርትና ምርታማነት በዘላቂነት እንዲሻሻል ለተፈጥሮ ሃብት፣ ለሥነ-ምህዳርና የአካባቢ አየር ተስማሚ ግብአቶች፣ ቴክኖሎጂዎች፣ ክህሎቶችና የመድህን አገልግሎቶች ተደራሽ የሚያደርግ ሥርዓት እንዲጠናከር ይደረጋል።

2. የግለሰቦችና ቤተሰቦች የገቢ፣ የስራ ፈጠራና የመግዛት አቅም እንዲሻሻልና የምግብ ምርቶች የገበያ ትስስር እንዲጠናከር ይደረጋል።

3. የሰብል፣ እንስሳትና ዓሳ ሃብት የጤና አገልግሎትና እንክብካቤ እንዲጠናከር ይደረጋል።

4. ፍትሃዊና የተመጣጠነ፣ የንጥረ-ምግብ ይዘታው የተሟላ፣ በቂና ደህንነቱ የተረጋገጠ የምግብ ክፍፍል፣ የገንዘብ ድጋፍና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማሻሻል የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞች እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

5. ለአካባቢ አየር ለውጥ መቋቋም፣ መላመድና ምላሽ መስጠት የሚያስችል የምግብ አመራረት ሥርአት በመዘርጋት ቤተሰቦች አደጋን የመቋቋም አቅማቸው እንዲጎለብት ይደረጋል።

6. ባዮቴክኖሎጂን በማያሰጋና ተገቢ በሆነ መልኩ ለምግብ ምርትና ዝግጅት ለመጠቀም የሚያስችል ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል።

## 7.2. ከእርሻ እስከ ጉርሻ ያለውን የምግብ ደህንነትና ጥራት ማረጋገጥ

የምግብ ደህንነት ሥርዓት ህብረተሰቡ ደህንነቱ ያልተጠበቀ ምግብ ከመመገብ ከመታደጉም ባሻገር ሀገሪቱ ከግብርና ምርቶች የተሻለ ጥቅም እንድታገኝ ያስችላል። በመሆኑም የሁሉንም ከእርሻ እስከ ጉርሻ የምግብ እሴት ሰንሰለት ተዋናዮችን ባሳተፈ መልኩ የምግብ ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ የምግብ ደህንነትና ጥራት አንድ የፖሊሲ አቅጣጫ እንዲሆን ተደርጓል።

## ዓላማ

የፖሊሲው ዓላማ በምግብ ሰንሰለት ውስጥ የምግብ ደህንነትና ጥራትን ማረጋገጥ ነው።

## ስልቶች

ከላይ የተጠቀሰውን አላማ ለማሳካት መንግሰት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገብራል።

1. ተቀዳሚ የግብርና ምርቶችንና የሚቀነባበሩ ምግቦች ደህንነትና ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል።

2. በምግብ ምርት ሰንሰለት ውስጥ የምግብን ደህንነትና ጥራት ለማረጋገጥ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎች እንዲያድጉና እንዲላመዱ እንዲሁም የምግብ ደህንነትና ጥራት እንዲጠበቅ ህጋዊ ማዕቀፍ እንዲዘረጋና እንዲተገበር ይደረጋል።

3. በተለያዩ የምግብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማለትም ሆቴሎች፤ ምግብ ቤቶች፤ በመንገድ ዳር ምግብ የሚሸጡና በሌሎች አካላት ተዘጋጅተው ለህብረተሰቡ የሚቀርቡ የምግብ ዓይነቶች ጥራትና ደህንነት እንዲጠበቅ ይደረጋል።

4. የተቀየጡ፣ የተጭበረበሩ፣ ተመሳስለው የሚቀርቡና ከደረጃ በታች የሆኑ ምግቦች ወደ ገበያ በመግባት ለህብረተሰቡ እንዳይቀርቡ የሚከላከል አሰራር እንዲዘረጋና እንዲጠናከር ይደረጋል።

5. የንፁህ ውሃ አቅርቦት፣ ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር የሚያጠናክር ሥርዓት ይዘረጋል።

## 7.3 የድህረ-ምርት አያያዝን ማሻሻል

በምግብ ሰንሰለት ውስጥ እያጋጠመ ያለውን የምግብ ምርት ብክነትና ደህንነት መቀነስን ለማሻሻል ወቅቱን ባገናዘበ ቴክኖሎጂ፣ ክህሎት፣ መሰረተ-ልማትና ግብዓት የታገዘ ዘመናዊ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም የድህረ ምርት አያያዝ ሥርዓት መዘርጋት እንደ አንድ የፖሊሲ አቅጣጫ ተወስዷል።

### ዓላማ

የፖሊሲው ዓላማ በምግብ ሰንሰለት ውስጥ የድህረ-ምርትን አያያዝ ለማሻሻል ነው።

### ስልቶች

ከላይ የተጠቀሰውን ዓላማ ለማሳካት መንግሰት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገብራል።

1. የምግብ ማቀነባበሪያ ቴክኖሎጂ ማሰልጠኛ ማዕከላትን በቤተሰብና በማህብረሰብ ደረጃ በሁሉም የሀገሪቱ አከባቢዎች እንዲገነቡና እንዲተገበሩ ይደረጋል።

2. የምግብ እሴትን ለመጨመር፣ የድህረ-ምርት አያያዝን ለማሻሻልና የቴክሎሎጂ ሽግግር እንዲተገበር አነስተኛ፣ መካከለኛና ትላልቅ የግብርና ምርቶች ማቀነባበርያ እንዱስትሪዎችና መሰረተ-ልማቶች እንዲገነቡ ይደረጋል።

## 7.4 በሁሉም የእድሜ ክልል ለሚገኙ ዜጎች ተገቢ ሥርዓተ-ምግብን ማረጋገጥ

የሥርዓተ-ምግብ መዛባት ችግርን ለመከላከል የሴክተሮች ውጤታማ የሆኑ ቀጥተኛና ሥርዓተ-ምግብ ተኮር ተግባራትን በጋራ ማቀድና መተግበር የተሻሻለ ሥርዓተ-ምግብ በሁሉም እድሜ ክልል ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲኖር በማድረግ የተሻለ ህይወት፣ ረጅም ዕድሜ ያለውና አምራች ዜጋ መፍጠር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ያጎናፅፋል። ይህንኑ ከግንዛቤ በማስገባት በሁሉም የእድሜ ክልል ለሚገኙ ዜጎች ተገቢ ሥርዓተ-ምግብን ማረጋገጥ እንደ አንድ የፖሊሲ አቅጣጫ ተደርጓል።

### ዓላማዎች

**ፖሊሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።**

1. የዜጎች በተለይም የነፍሰ-ጡርና የሚያጠቡ እናቶች፣ ልጆችና አፍላ ወጣቶች ሥርዓተ-ምግብ ሁኔታን ማሻሻል።
2. በተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎችንና በተለያዩ አጋጣሚዎች የተጎዱና ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታን ማሻሻል።

### ስልቶች

ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካት መንግስት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገብራል።

1. የእናት ጡት ወተትንና ተጨማሪ የበለጸጉ የህፃናት ምግቦችን የሚጠብቅና የሚያበረታታ ሥርዓት እንዲዘረጋና እንዲጠናከር ይደረጋል።

2. የጥቃቅን ንጥረ-ምግቦች እጥረትና ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችል የምግብ ማበልጸግያና የተመጣጠነ የምግብ አቅርቦትን የሚያረጋግጥ ሥርዓት እንዲዘረጋና እንዲጠናከር ይደረጋል።

3. ሁሉን አቀፍና የተቀናጀ የሥርዓተ-ምግብ አገልግሎት በትምህርት ቤቶች፣ ልዩ የሥርዓተ-ምግብ ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችና ለተላላፊና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የሚሰጥ የሥርዓተ-ምግብ አገልግሎት እንዲጠናከር ይደረጋል።

4. የሴቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት የሚያዳብርና ጉልበትና ጊዜ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሴቶችን የስራ ጫና የሚቀንስ ስርአት እንዲዘረጋና እንዲጠናከር ይደረጋል።

5. የአካባቢን ሁኔታ መሰረት ያደረገ ሥርዓተ-ምግብ ተኮር የጤናና የሥርዓተ-ምግብ አገልግሎት ተደራሽነት እንዲጠናከር ይደረጋል።

6. ሁሉን አቀፍ የውሃ፣ የአካባቢና የግል ንፅህና ተቋማትና አገልግሎት ተደራሽነትና ተጠቃሚነት እንዲጠናከር ይደረጋል።

7. የነፍሰ ጡርና የሚጠቡ እናቶች፣ ልጆችና አፍላ ወጣቶችን የአመጋገብ ባህልና የአመጋገብ ስርዓት ንቃተ ህሊና ለማሻሻል ተስማሚና አገር በቀል የማህበራዊና የባህርይ ለውጥ የተግባቦት ዘዴዎች በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። ለዚህም ራሱን የቻለ ማስፈጸሚያ ስልት ይነደፋል።

## 7.5 ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ፈጣንና ተገቢ የምግብና የሥርዓተ-ምግብ ምላሽ መስጠት

የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በሚያጋጥሙበት ወቅት የቅደመ-ማስጠንቀቂያ፣ የዝግጁነትና ክትትል ሥርዓቱን ማጠናከር፣ ፈጣን ምላሻ መስጠትና ተጎጂዎችን መልሶ ማቋቋምና ሊከሰቱ የሚችሉትን የአጭርና የረጅም ጊዜ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ አደጋዎችን መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የምግብና የሥርዓተ-ምግብ ምላሽ መስጠት እንደ አንድ የፖሊሲ አቅጣጫ ተደርጓል፡፡

### ዓላማ

የፖሊሲው ዓላማ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክንያት ለሚፈጠሩ የምግብና የሥርዓተ-ምግብ ችግሮች ፈጣንና ተገቢ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አገራዊ አቅምን ማጠናከር ነው፡፡

### ስልት

ከላይ የተጠቀሰውን ዓላማ ለማሳካት የሚከተለው ስልት ይተገበራል፡፡

1. በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክንያት ለሚፈጠሩ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ችግሮችና የተጋላጭነት መንስኤዎችን በመለየት የቅደመ-ማስጠንቀቅያ፣ ዝግጁነትና ወቅታዊና ተገቢ ምላሽ የሚሰጥ ሥርዓት እንዲዘረጋና እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡

## 7.6 የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተግባቦትን ማጠናከር

የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተግባቦት ማለት ምግብና ሥርዓተ-ምግብን በተመለከተ በህብረተሰቡ ውስጥ ተፅእኖ በመፍጠር፣ የህብረተሰብ ንቅናቄና የባህርይ ለውጥ በማምጣት የሥርዓተ-ምግብ ዕውቀት ያለው ማህበረሰብን ማፍራት ነው። ስለሆነም የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተግባቦት ማጠናከር እንደ አንድ የፖሊሲ አቅጣጫ ተደርጓል።

### ዓላማ

ፖሊሲው የሚከተለው ዓላማ አለው፡-

1. በመረጃ ላይ የተመሰረተ የሥርዓተ-ምግብ አገልግሎት አጠቃቀም እንዲኖር ለማድረግ በምግብ ሰንሰለት ውስጥ የግለሰብ፣ ቤተሰብና ማህበረሰብ እውቀት እንዲሻሻል ማድረግ።

### ስልቶች

ከላይ የተጠቀሰውን ዓላማ ለማሳካት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገበራሉ።

1. በስራ ላይ የዋሉና ገና ያልታወቁ የግንኙነትና ተግባቦት አማራጮችን በመጠቀም በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተፅእኖ ፈጣሪዎችና ውሳኔ ሰጪዎች አቅም የሚገነባበት ሥርዓት እንዲዘረጋና እንዲጠናከር ይደረጋል።
2. ባህላዊና አካባቢያዊ ተቀባይነት ያላቸው የማህበራዊና የባህርይ ለውጥ የተግባቦት ዘዴዎች ጥቅም ላይ በማዋል ሞዴል ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች የሚፈጠሩበት ሥርዓት እንዲዘረጋና እንዲጠናከር ይደረጋል።

## 7.7 የምግብና ሥርዓተ-ምግብ አስተዳደር ማቋቋምና ማጠናከር

የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲው በሀገሪቱ የብዙ-ሴክተሮች የምግብና ሥርዓተ-ምግብ አስተዳደር ተግባራት የፖሊሲ ማዕቀፍ ይሰጣል። የኢትዮጵያ መንግስት ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ የሚዘረጋ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲውን ትግበራ የሚመራና የሚያስተዳድር በከፍተኛ የመንግስት ስራ ሃላፊዎች የሚመራ አስተዳደራዊ አካልና መዋቅር ያቋቁማል። በተጨማሪም የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲውን ተግባሪ ሴክተሮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት አቅም ለመገንባት አቅጣጫ ያስቀምጣል። የምግብና ሥርዓተ-ምግብ አስተዳደሩ ለምርምርና ፈጠራ፣ በቂ ሃብት ለመመደብ እንዲሁም ለክትትልና ግምገማና ተጠያቂነትን ለሚያሰፍን ማዕቀፍ ልዩ ትኩረት ይሰጣል። በመሆኑም የምግብና ሥርዓተ-ምግብ አስተዳደር ማቋቋምና ማጠናከር እንደ አንድ የፖሊሲ አቅጣጫ ሆኖ እንዲወጣ ተደርጓል።

### ዓላማዎች

ፖሊሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ለምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲው ተግባሪ ሴክተሮች ቅንጅታዊ አሰራርና አፈፃፀምን የሚያጠናክር አስተዳደር እንዲኖር ማድረግ።

2. የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲውን ትግበራ ለማሳካት ከመንግሥት ካዝና፣ ከልማት አጋሮችና ሌሎች አዳዲስ አማራጮችን በመጠቀም ዘላቂ የፋይናንስ ምንጭ እንዲኖር ማድረግ።

3. የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲው ተግባሪ ሴክተሮችን ተቋማዊ አቅም በሰው ሃይል፣ በምርምርና በቴክኖሎጂ እንዲጠናከር ማድረግ።

4. ውሳኔ ሰጭነትን የሚያሳድጉ፣ ትምህርታዊ ጠቀሜታ ያላቸውና ተጠያቂነትን የሚያሰፍኑ መረጃዎች እንዲጠናቀሩ ማድረግ።

## ስልቶች

ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካት መንግሥት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገብራል።

1. ሙሉ ስልጣን፣ ተጠያቂነት፣ ህጋዊ ማዕቀፍና አሰሪ መዋቅር ያለው የምግብና ሥርዓተ-ምግብ አስተዳደር ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ በየደረጃው ይቋቋማል።

2. በሁሉም ደረጃ ከምግብና ሥርዓተ-ምግብ ጋር የተያያዙ ምርምሮች፣ ስልጠናዎች፣ አገልግሎቶችና አሰራሮች አቅም በግለሰብ፣ በማህበረሰብና በተቋም ደረጃ እንዲጠናከር ይደረጋል።

3. በመረጃ ተግባቦትና ቴክኖሎጂ የሚደገፍና ተጠያቂነት የሰፈነበት ጠንካራ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት በመፍጠር ፖሊሲው ይተገበራል።

4. ከመንግሥት፣ ከህብረተሰቡ፣ ከግል ባለሃብቱ፣ ከልማት አጋሮች ወይም ሌሎች ሃገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለማቀፋዊ ተቋማትና ድርጅቶች ጥብቅ ትስስር በመፍጠር በቂ የትምህርት፣ የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግርና የሀብት ማሰባሰብና መመደብ ሥርዓት እንዲፈጠር ይደረጋል።

# 8 የፖሊሲው ትግበራ

የፖሊሲው ትግበራ መረጃን መሰረት ያደረገ አካሄድና የትግበራ ማዕቀፍ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ዘላቂነትን፣ ወጪ ቆጣቢነትን፣ ቅንጅታዊ አሰራርንና የማህበረሰብ ተሳትፎን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ቁልፍ አካሄዶች እንደሚከተለው ይሆናሉ።

## 8.1 አካሄዶች

### 8.1.1 የሕይወት ኡደት አካሄድ

ይህ ፖሊሲ የሕይወት ኡደት አካሄድን የሚከተል ሲሆን የሥርዓተ-ምግብን ጉዳይ በሁሉም የዕድሜ ደረጃ ከሁሉም የትውልድ ዘመን አንፃር የሚያይ ነው። ፖሊሲው በተለይ ወሳኝ በሆኑት በመጀመሪያዎቹ 1000 ቀናት ማለትም ከፅንሰት እስከ ሁለት ዓመት ባሉ ህፃናት ላይ ትልቅ ትኩረት ያደርጋል። በእነዚህ 1000 ቀናት የሚደረገው የተስተካከለ ሥርዓተ-ምግብ በህፃናቱ የህይወት ዘመን ሁሉ ዘላቂ የሆነ ዕድገትና አዎንታዊ የአካልና የአእምሮ ዕድገት የሚያመጣና የወደፊት ሕይወታቸውን ብሩህ የሚያደርግ ነው። ይህ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ በፅንስ፣ ጨቅላነት፣ ህፃንነትና በአፍላ ወጣትነት ወቅት የሚተገበር መርሃ-ግብር ከአመጋገብ ጋር የተያያዙ ችግሮችን፣ ሥር-ሰደድ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችንና የአካል ጉዳቶች እንዲሁም ሞት በቀጣይ የሕይወት ደረጃዎች እንዳይከሰቱ ለማድረግ ያስችላል።

## 8.1.2. ምግብ እንደ ሰብአዊ መብት

የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትና መረጋገጥ የሁሉም ዜጎች ሰብአዊና ሕገ-መንግስታዊ መብት ነው። የሚሰጡ አገልግሎቶችም የሁሉንም ዜጎች የሰብአዊ መብቶች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። በመሆኑም በሁሉም የህይወት ዑደት ደረጃ ውስጥ የሚያልፉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የሥርዓተ-ምግብ ፍላጎታቸውን በማሟላት ለተሟላ ጤንነታቸው ሊረዳ የሚችል በማንኛውም ጊዜ ደህንነቱ የተጠበቀ፤ በቂና ጥራት ያለው ምግብ ማግኘት እንዳለባቸው በዚህ ፖሊሲ ተቀምጧል።

## 8.1.3. ምግብን መሰረት ያደረገ አካሄድ

ይህ ፖሊሲ የሥርዓተ-ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ምግብን መሰረት ያደረገ የሥርዓተ-ምግብ አካሄድ ተግባራዊ ያደርጋል። ይህም አካሄድ በተለየ መልኩ የሚያየው የጥቃቅን ንጥረ-ምግብ ጉዳዮችን፣ የእንስሳትና የዓሳ ምርቶችን ማቀነባበርንና በንጥረ-ምግቦች የበለፀጉ ምግቦች ተጠቃሚነትን ማሻሻል ነው። የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲው ማህበረሰቡ ጤናማ የሆኑ ምግቦችን ከተለያዩ የምግብ ክፍሎች መርጦ እንዲመገብ በማስቻል ለሥርዓተ-ምግብ ዋስትና የረዥምና ዘላቂ መፍትሔ ያመጣ ዘንድ የምግብ-ተኮሩን አካሄድ ያበረታታል።

## 8.1.4. የባለድርሻ አካላትን ትብብር፣ ቅንጅትና ትስስር ያረጋገጠ አካሄድ

ሥርዓተ-ምግብ በተፈጥሮው በሚያመጣው ውጤትም ሆነ ተፅእኖ ፈርጀ ብዙና የብዙ ባለድርሻ አካላት ጉዳይ ነው:: ፖሊሲው ወቅቱን ጠብቆ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈፀም የባለድርሻ አካላትን

ትብብር፤ ቅንጅትና ትስስር ማረጋገጥ እንዲቻል የሚያግዝ የትግበራ ማዕቀፍ እንዲሁም አግባብ ያለው አመራርና የማስፈፀም አቅም ያስፈልገዋል። በምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ ትግበራ የባለድርሻ አካላትን ትብብር፤ ቅንጅትና ትስስርን ለማቀላጠፍ እንዲረዳ መንግሥት ምቹ ሁኔታንና የግብረ-መልስ ሥርዓቶችን ይፈጥራል።

## 8.1.5. ቀጥተኛና ሥርዓተ-ምግብ ተኮር ትግበራ

መንግስት ከቀጥተኛና ሥርዓተ-ምግብ ተኮር ተግባሪ ሴክተሮች የወጡ የሥርዓተ-ምግብ ግቦችንና ተግባራትን በማካተት የሥርዓተ-ምግብ አለመመጣጠን መንስኤዎችን ለመቅረፍ የሚረዱ ተግባራትን ያበረታታል።

ሁሉንም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሴክተሮች በሥርዓተ-ምግብ እይታ በመቃኘት ቀጥተኛና ሥርዓተ-ምግብ ተኮር መርሐ-ግብሮችን በመቅረፅ እንዲተገበሩ ይደረጋል።

## 8.1.6. ከእርሻ እስከ ጉርሻ አካሄድን ታሳቢ ያደረገ ትግበራ

የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በእርሻ፣ በምግብ ማቀነባበር፣ በምግብ መጓጓዝና ማከማቸት፣ በተለያዩ የምግብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና በመንገድ ዳር ለሽያጭ ሲቀርብ እንዲሁም በቤት ውስጥ ምግብ በማዘጋጀትና በመመገብ ሂደት ውስጥ የምግብ ብክነትን መቀነስ፣ ጥራቱንና ደህንነቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የምግብ አምራቹን፣ አቀነባባሪውን፣ አጓጓዡን፣ አከማቹን፣ ሻጩንና ተጠቃሚውን የምግብ ብክነትን እንዲቀንስና ደህንነትና ጥራት እንዲረጋገጥ በምግብ ስርጭት ሰንሰለት ውስጥ ወሳኝ ሚናን ሊጫወቱ የሚችሉ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ ሁሉን አቀፍና የተቀናጀ ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል።

## 8.2. የህግ ማዕቀፍ

የኢትዮጵያ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ በሀገሪቱ ለሚታለመው የሥርዓተ-ምግብ ዕቅድ፣ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም ትብብር አስፈላጊ የህግና ተቋማዊ ማዕቀፍ ይሰጣል። ይህ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ በተሳካ መልኩ እንዲፈፀም የኢትዮጵያ መንግሥት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።

1. ለምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ ትግበራና ቁጥጥር የሚረዳ በሁሉም የአስተዳደር እርከን ደረጃዎች ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ ህጋዊ ማዕቀፍና ተቋም እንዲመሰረት ይደረጋል።

2. ሁሉም ኢትዮጵያውያን በቂ የሆነ ምግብ የማግኘት መብታቸውን ለማስከበርና የምግብ ደህንነትና ጥራት ለማረጋገጥ ሥርዓተ-ምግብን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ መመዘኛዎች፣ ውሎች፣ ስምምነቶች፣ ህጎችና ደንቦችን በመከተል አሁን በስራ ላይ ያሉትን ህጎች እንዲከለሱና አዳዲስ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ወጥተው ስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

## 8.3. ተቋማዊ አደረጃጀት

ምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዘርፈ ብዙና ሁሉንም ሴክተሮችና ባለድርሻ አካላትን የሚመለከት ጉዳይ ነው። በመሆኑም የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ በመቀመር በተሻለ ተግባቦትና በሴክተሮች ትብብር የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ ትግበራን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ቅንጅታዊ ስራን የሚያስተባብር አካል ያስፈልጋል። በዚህም መሰረት በብሔራዊ ደረጃ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ ትግበራን ለማስተባበርና ለማሳለጥ እንዲረዳ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ምክር ቤት እንዲቋቋም ይደረጋል። ምክር ቤቱ ምግብንና ሥርዓተ-ምግብን የሚያስተባብር ተቋም የሚያቋቁም

ሲሆን ይህም ተቋም የራሱ የሆነ አደረጃጀትና መዋቅር ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ጉዳዮችን በሚመለከት የመንግስት አማካሪ አካል ሆኖ እንዲያገለግልና ሁሉንም ሴክተሮችንና ባለድርሻ አካላትን እንዲያስተባብር ይደረጋል፡፡

የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ምክር ቤት አመራርና አባላት በብሔራዊ ደረጃ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየም ሲሆን ስራውን ለማሳለጥም ሴክሬታሪያት ይኖረዋል፡፡ የአስተዳዳሪው አካል አባላትም በመንግሥት የሚወሰን ይሆናል፡፡ በክልል ደረጃም በክልል ፕሬዝዳንት በሚሰየም ሰብሳቢ የሚመራና ተጠሪነቱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሚሰይሙት አካል የሆነ የክልሎች የምግብና ሥርዓተ-ምግብ የበላይ አስተዳዳሪ አካል ይቋቋማል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም በዞንና በወረዳ ደረጃ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ የበላይ አስተዳዳሪ አካላት የሚቋቋሙ ሲሆን በዞንና በወረዳ አመራሮች ወይም አስተዳዳሪዎች ሰብሳቢነት የሚመሩ ይሆናሉ፡፡ በቀበሌ ደረጃ የሚቋቋሙ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ኮሚቴዎችም በቀበሌ አመራሮች ሰብሳቢነት የሚመሩ ይሆናሉ፡፡

## 8.4. የአቅም ግንባታ

በምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዙሪያ የሚተገበሩ የአቅም ግንባታ ስራዎች የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተግዳሮቶችን ሊቀርፉ የሚችሉ የብሔራዊ፣ ክልላዊና ተቋማዊ አቅሞችን ለማጠናከር አስፈላጊ ናቸው፡፡ ስለሆነም ፖሊሲው በስልጠና፣ በጥናትና ምርምር፣ በማህበረሰብ አገልግሎቶች፣ ስልቶችና መርሀ-ግብሮች ቀረፃ፣ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ ትኩረት ይሠጣል፡፡

### 8.4.1 የሰው ኃይል

ፖሊሲውን በሁሉም ደረጃ ለመተግበርና የአሰራር ሥርዓትን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር የተቋማትን፣ የሰው ሃብት፣ የግለሰቦችንና እንዲሁም

የማህበረሰብን አቅም ግንባታ ስራ ትኩረት ይሰጠዋል። ሴቶች ለሥርዓተ-ምግብ ችግሮች በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ መሆናቸውን በመረዳት ችግሩን በዘለቄታዊ እንዲወገድ መፍትሔ በማምጣት ሴቶች ቁልፍ ተዋናይ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሴቶችን፣ የሴቶች አደረጃጀቶችና ማህበራትን፣ የሴቶች የልማት ቡድኖችን አቅም ማጎልበት ትኩረት ይሰጠዋል። የሰው ኃይል የአቅም ግምባታ ሥራዎችን ለማጠናከር የሚከተሉት ስልቶች ይተገበራሉ።

1. የአጭርና ረዥም ጊዜ አጠቃላይ የሆነ የምግብና የሥርዓተ-ምግብ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ስልት ተዘጋጅቶ እንዲተገበርና እንዲጠናከር ይደረጋል።

2. የከፍተኛ ትምህርት እና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት የምግብና ሥርዓተ-ምግብ የስልጠና መስክ እንዲከፍቱና ባለሙያዎችን ማሰልጠን እንዲችሉ ይደረጋል።

3. የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ትምህርቶች መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት ተቋማት ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ተካቶ እንዲሰጥ ይደረጋል።

4. ለምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲ ትግበራ መርሀ-ግብር አመራርና አስተዳደር፣ ተቋማዊ መዋቅር፣ የአሰራር ሥርዓትና የማስፈጸም አቅም እንዲገነባ ይደረጋል።

5. በሁሉም ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሴቶች፣ የሴቶች አደረጃጀቶችና የሴቶች የልማት ቡድኖች የአቅም ግንባታ እንዲጠናከር ይደረጋል።

## 8.4.2. የስልጠናና ምርምር ተቋማት

1. በሀገር አቀፍና በክልሎች ደረጃ ጠቀሜታ ያላቸውን በምግብና ሥርዓተ-ምግብ ችግሮች ላይ ያተኮሩ ምርምሮችን ለመተግበር የምርምር ተቋማት አቅምን በማጎልበት ለፖሊሲ ክለሳ የሚረዱ አዳዲስ ሳይንሳዊ መረጃዎችን ለማቅረብ የሚያስችል አቅም እንዲጠናከር ይደረጋል።

2. በምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዙሪያ ካደጉ ሀገሮች የምርምርና ከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነት በመፍጠር የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ምርምር የልህቀት ማዕከላት እንዲቋቋሙ ይደረጋል።

3. የከፍተኛ ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት የምግብ፣ የሥርዓተ-ምግብ፣ የምግብ ደህንነትና ጥራት እንዲሁም የድህረ-ምርት አያያዝ ላይ ያተኮረ ብሔራዊና ክልላዊ የምርምር ፍላጎትን ማሟላት እንዲችሉ አቅማቸው እንዲጠናከር ይደረጋል።

4. ሀገራዊ የልማት ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ምርምር፣ የመረጃ ቋት ምስረታ፣ የሰው ሃይል ልማት፣ መሰረተ ልማት፣ ለትምህርትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች በጀት እንዲመደብ ይደረጋል።

## 8.4.3. የቁጥጥር አካላት

የቁጥጥር አካላት አቅም በሀገር አቀፍ ደረጃ፣ በክልሎች፣ በገጠርና ከተማ አካባቢዎች እንዲሁም በወደብ አካባቢ በሰው ኃይል፣ በመመርመሪያ መሳሪያ፣ በላቦራቶሪና በሌሎች አስፈላጊ ግብዓቶች እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

## 8.5. የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተግባቦት

የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተግባቦት ተሳታፊዎች በሥርዓተ-ምግብ፣ በምግብና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ በነፃነት ዕውቀትን፣ እሴቶችንና ልምዶችን የሚለዋወጡበት የሁለትዮሽ ሂደት ነው። ይህ ተግባቦት በውሳኔ ሰጭነት እንዲሁም ተጠቃሚዎችን በማበረታታት የሥርዓተ-ምግብ መረጃ ግብዓቶችንና አገልግሎቶችን ተደራሽ በማድረግ የሥርዓተ-ምግብ ተግባራት ውስጥ መሳተፍ ያለባቸውን ሰዎች ሚና የሚያረጋግጥ ነው። የሰቆጣ ቃልኪዳን እንደ ማህበራዊ ተግባቦት ንቅናቄ መነሻ በመጠቀም የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተግባቦት በሀገር አቀፍ ደረጃ ማህበራዊ ንቅናቄው እንዲስፋፋ ይደረጋል።

የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተግባቦት ትኩረት የሚያደርግባቸው ቁልፍ ጉዳዮች የእናቶች፣ የጨቅላ ህፃናት፣ የህፃናትና የአፍላ ወጣቶች ሥርዓተ-ምግብ ትግበራን ከፍተኛ ደረጃ ማድረስ፣ ሥር-ሰደድ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል፣ የድህረ-ምርት አያያዝን ማሻሻል፤ በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃ ያለ የምግብ ስብጥርና ከእርሻ እስከ ጉርሻ እንዲሁም የምግብ ደህንነትንና ጥራት አካሄድን በመጠቀም ሁሉንም የምግብ ምርት ደረጃዎች ትግበራን ከፍ ማድረግ ነው። የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤትና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ፤ የግልና የሲቪክ ማህበራት የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተግባቦት ስራዎችን እንዲያስተባብሩና እንዲደግፉ ይደረጋል። በሁሉም ሂደት ውስጥ የሴቶችና የሴቶች አደረጃጀት ሚና እንዲጎላ ይደረጋል። ከላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ዝርዝር የሥርዓተ-ምግብ ተግባቦትና ማህበራዊ ንቅናቄ ስትራቴጂም ተዘጋጅቶ ይተገበራል።

## 8.6. ዘላቂ የገንዘብ ምንጭ

የፖሊሲውን ግቦች ለማሳካት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይና መሰረተ-ልማት ያስፈልጋል። የመሰረተ-ልማቱና የመዋዕለ ንዋዩም ምንጭ ከመንግሥት፣ ከግል ባለሃብቱ፣ ከአጋር ድርጅቶችና ከማህበረሰቡ ተሳትፎ የሚገኝ ሲሆን መንግሥት ከህዝቡና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ውጤታማ በሆነ መልኩ ለፖሊሲው ትግበራ መዋሉን ያረጋግጣል። ለፖሊሲው ውጤታማነት በግል ባለሃብቱ፣ በምግብ ኢንዱስትሪዎች፣ በሰፋፊ እርሻዎች፣ በምግብ አስመጪና ላኪዎች፣ በምግብ ማቀነባበሪያዎችና ማበልፀጊያዎች የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይደረጋል። በፖሊሲው ትግበራ ላይ የህብረተሰቡን ንቅናቄ በመፍጠር በንቃት እንዲሳተፉና ሁሉን አቀፍ ድጋፍ አንዲያደርጉ ይደረጋል።

# 9 ለሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ምላሽ ሰጪነት

በሀገራችን በምግብ ዋስትና አለመረጋገጥና በሥርዓተ-ምግብ መዛባት በእጅጉ ከሚጠቁ የህብረተሰብ ክፍሎች ከህፃናት ቀጥለው ሴቶችና አፍላ ወጣት ሴቶች ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ። ለዚህ ችግር የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መጓደል እንደ ቀዳሚ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መጓደል በቤተሰብ ደረጃ በወንዶችና ሴቶች መካከል የሚኖረውን ፍትሀዊ የምግብ ክፍፍልን በማዛባት ሴቶችንና አፍላ ወጣት ሴቶችን ለከፋ የሥርዓተ-ምግብ መዛባት ችግሮች በእጅጉ ሊያጋልጣቸው ይችላል።

የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መጓደል ለሥርዓተ-ምግብ መዛባት መንስኤውም ውጤትም ሊሆን ይችላል። የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመረጋገጥ በአጭር ጊዜ ለሚከሰትም ሆነ ሥር-ሰደድ ከሆነ ከፍተኛ የሥርዓተ-ምግብ መዛባት ጋር ይያያዛል። ሁለቱም ችግሮች በቤተሰብና በማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤና የህይወት ዑደቶች ጋር በጣም የተቆራኙ ናቸው። የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መተግበርና የሴቶችና አፍላ ወጣት ሴቶች ሥርዓተ-ምግብ ማሻሻል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈውን የሥርዓተ-ምግብ መዛባት ዑደት ለመስበር ከፍተኛ ሚና አለው።

ስለሆነም የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፓሊሲ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት፣ ልዩነትና አድልዎ በሴቶችና አፍላ ወጣት ሴቶች ሊያደርስ የሚችለውን የሥርዓተ-ምግብ መዛባትን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሥርዓተ-ፆታን ባማከለ መልኩ

በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ ውጤታማ የሆኑ የሥርዓተ-ምግብ ስራዎች እንዲተገበሩ ያደርጋል። በመሆኑም የስርዓተ-ፆታን ትግበራ ለማሳካት የሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች ማለትም የሴቶች፣ ልጃገረዶች፣ ወንዶች፣ የተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦችና የማህበረሰቡ ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖር ይደረጋል።

# 10 የባለ ድርሻ አካላት ሚና

## 10.1 የመንግስት ሚና

መንግሥት ለምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፖሊሲው ትግበራ የሚያስፈልገውን መዋዕለ ንዋይ በማሰባሰብ እንዲሁም የፋይናንስ፣ የቴክኒክ፣ የህግና የመሰረተ ልማት ድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት የአመራር ሚናውን በቁርጠኝነት ይወጣል። በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላትም ከፖሊሲው የሚመነጩ ድርሻዎቻቸውን እንዲተገብሩ ይደረጋል።

## 10.2 መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ሚና

በምግብና ሥርዓተ-ምግብ የስራ መስክ የተሰማሩ መንግሰታዊ ያልሆኑ አካላት ያላቸውን የሰው ሃይል፣ የፋይናንስና የመሰረተ-ልማት አቅም አቀናጅተው የኢትዮጵያ መንግሥት ፖሊሲውን ለመተግበር የሚያደርገውን ጥረት ይደግፋሉ።

## 10.3 የግል ባለሃብቱ ሚና

ከእርሻ እስከ ጉርሻ ባለው የምግብ ስርጭት ሰንሰለት ውስጥ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ምግብን ለብክነት የማያጋልጡና የምግብ ጥራትና ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶች ለመዘርጋት ሚናቸውን ይወጣሉ።

## 10.4 የህብረተሰቡ ሚና

ለምግብና የሥርዓተ-ምግብ ዋስትና መረጋገጥ የህብረተሰብ ሁሉን አቀፍ ተሳትፎና ባለቤትነቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

# 11 ክትትልና ግምገማ

ለፖሊሲው ትግበራ ውጤታማ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል። የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ከፖሊሲው ስልቶች ላይ የሚመነጩ መርሃ-ግብሮችን አተገባበርና ውጤታማነት በንፅፅር ሊያሳዩ በሚችሉና በቅድሚያ በሚለዩ ጠቋሚዎች አንፃር ይገመገማል። የፖሊሲው ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ከሌሎች መሰል የግምገማና መረጃ ሥርዓቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዲኖረውም ይደረጋል። ሌሎች ሴክተሮችም በራሳቸው መርሃ-ግብሮች ውስጥ የሚተገበሩትን የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ሥራዎች እንዲገመግሙ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ስኬታማና ውጤታማ ተሞክሮዎችን በመለየት በፖሊሲው ላይ ምክንያታዊ ክለሳ ለማካሄድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

## የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱን ለማጠናከር፡-

ብሔራዊ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ የበላይ አስተዳዳሪ አካል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውጤታማ ትብብር በማድረግ ከፌደራል እስከ ቀበሌ በሚገኙ የመንግስት አስተዳደር እርከኖች ሁሉ በየተወሰኑ ጊዜ ገደቦች በፖሊሲው የተጠቀሱ ስልቶችና መርሃ-ግብሮች ትግበራ የተመዘገቡ ለውጦችን ይከታተላል።

ለፖሊሲው ትግበራ ክትትልና ግምገማ ውጤታማነት የዝርዝር ስራዎች አፈፃፀም ጠቋሚዎችና ኢላማዎች በክትትልና ግምገማ ስርዓት ውስጥ ተካተው

እንዲተገበሩና አፈፃፀማቸው ከቀበሌ እስከ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባለው የመንግስት የአስተዳደር እርከን እንዲገመገሙ ይደረጋል።

ቀጣይነት ያለው የምግብና ሥርዓተ-ምግብ የመረጃ ቅኝትና ዳሰሳ እንዲካሄድ እንዲሁም መረጃ ማጠናቀሪያ ሥርዓት እንዲዘረጋና እንዲጠናከር ይደረጋል።

# 12 የቃላት ፍቺዎች

1. **ምግብ** – ማንኛውም በአንድ ሀገር ውስጥ እንዲበላ የተፈቀደ ምግብና መጠጥ።

2. **ሥርዓተ-ምግብ** – ምግብ መመገብን፣ የምግብ መፈጨትን፣ ምግብ በሰውነት ውስጥ መዋሃድንና የንጥረ-ምግቦች ጥቅም ላይ መዋልን ይህም ውህደት ለሰውነት አካላዊና አዕምሮአዊ ዕድገትና ብልፅግና፣ በሽታ የመከላከልና የመቋቋም ሂደትን የሚያጠና ሳይንስ ነው።

3. **ንጥረ - ምግብ** – በምግብ ውስጥ የሚገኙ ኬሚካሎች ሲሆኑ ለሰውነት ሀይል፣ ለህዋሶች መታደስ፣ በሰውነት ውስጥ የሚገኙ ቅመሞች በትክክል እንዲሰሩና ትክክለኛ የሰውነት እድገት እንዲኖር ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ በምግብ ውስጥ የሚገኙ ንጥረ-ነገሮች ናቸው።

4. **ሥርዓተ-ምግብ ዋስትና** – ሁሉም ሰው በማንኛውም ጊዜ ፍላጎቱንና ምርጫውን የሚያሟላ ጤነኛና ብሩህ ህይወት እንዲኖረው ጥራቱን የጠበቀና በአይነት፤ በስብጥር፤ በደህንነትና በንጥረ-ምግብ ይዘቱ በቂ የሆነ ምግብ የማግኘት እንዲሁም በቂ የጤና ክብካቤ፤ በቂ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና ጽዱ የመኖሪያ አካባቢ፤ በቤተሰብና ማህበረሰብ ደረጃ ስለ ሕጻናት ክብካቤ፤ ስለ ምግብ አዘገጃጀትና አያያዝ በቂ እውቀት የማግኘት ሁኔታ ማለት ነው።

5. **ምግብ ዋስትና –** የምግብ ዋስትና ማለት ሁሉም ሰው ጥራት ያለውና ጤነኛ ህይወት ለመምራት እንዲሁም የቀን የምግብ ፍላጎቱንና የምግብ ምርጫውን የሚያሟላ በቂ፤ የተመጣጠነና ደህንነቱ የተረጋገጠ ምግብ በማንኛውም ጊዜ ለማግኘት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ከባቢያዊ ተደራሽነት ሲኖረው ነው።

6. **የምግብ ሰንሰለት –** ማለት ከእርሻ እስከ ጉርሻ ያለውን የምግብ ስርጭት የሚያጠቃልል ሲሆን በእርሻ ወይም በእርባታ፣ በምግብ ማቀነባበር፣ በምግብ መጓጓዝና ማከማቸት፣ ለሽያጭ ማቅረብ እንዲሁም በተለያዩ የምግብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ የምግብ ዝግጅት፣ በመንገድ ዳር ምግብን ማዘጋጀት፣ በቤት ውስጥ ምግብን ማዘጋጀትና መመገብ ማለት ነው።

በምግብና ሥርዓተ-ምግብ ራሷን የቻለች
ሀገር ለመፍጠር እንተጋለን!